# አስቸኳይ መልእክት በአማራ ሕዝብ ስም ለተቋቋሙ ድርጅቶች በሙሉ!

የአማራ ሕዝብ በጥፋት ኃይሎች የዘር ማጥፋት አዋጅ ታውጆበት በግልጽና በስውር በሚወሰድበት ኢሰብአዊና አረመኔያዊ እርምጃዎች በየዕለቱ እንደቅጠል እየረገፈና ለአስከፊ ስቃይና መከራ እንደተዳረገ እየተመለከተና እያወቀ በከፍተኛ አስደናቂ የኃላፊነት ስሜት ዝም ብሎ እንዲመለከት ካደረገው እጅግ ያለቅጥ ከሰፋውና ፍጹም አግባብነት ከሌለው ትዕግሥቱ ወጥቶ ወያኔን፣ ኦነግን፣ ሸአቢያን ከመሳሰሉ የጥፋት ኃይሎች ከታወጀበት የዘር ማጥፋት ጥቃት እራሱን ለማዳን መንቀሳቀስ መጀመሩ የጥፋት ኃይሉን ወያኔንና ግብረአበሮቹን እጅግ በከፍተኛ ደረጃ አስደንግጧል፣ አሳስቧል፣ አሥግቷል፡፡

እንደ የጥፋት ኃይሎች ግምት የአማራ ሕዝብ እንዳያንሠራራ ተደርጎ አከርካሪው የተሠበረና ቀስ ዘና ብለውም በሚታወቅና በማይታወቅ፣ በግልጽና በስውር በየዕለቱ በሚወስዱት እርምጃ ምጥጥ እርግፍ አድርገው እንደሚጨርሱት እንደሚፈጁት ለራሳቸው እርግጠኛ ሆነው በዚህ መልኩ ሥራቸውን እየሠሩ ባሉበት ሁኔታ ነው እግዚአብሔር ብሎ የነቃው፡፡ ምንም እንኳ አሁንም ቢሆን በአማራ ሕዝብ ላይ ያለው መነቃቃት በሚፈለገው ደረጃ ላይ ያለ መሆኑ የሚያጠያይቅ ቢሆንም ቅሉ፡፡

የጥፋት ኃይሎች ሥጋት እጅግ እንዲያይል ያደረገው ደግሞ ይህ የአማራ ሕዝብ መነሣሣት አንዴ ከተቀሰቀሰ እነሱን ጠራርጎ ሳይቀብር እንደማይመለስ እርግጠኛ መሆናቸው ነው፡፡ በመሆኑም ይህ የተቀሰቀሰውን የአማራን ሕዝብ ራሱን የማዳን፣ ህልውናውን የማስቀጠል የሞት ሽረት ትግልን ያለ የሌለ ሁለንተናዊ አቅማቸውን አሟጠው በመጠቀም አኮለሽቶ፣ አጨናግፎ ለማስቀረት እረፍት የለሽ በሆነ ከፍተኛ ጥረት ተጠምደዋል፡፡ በዚህ መሠረት እየተወሰዱ ካሉ እርምጃዎች ውስጥ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅና የጅምላ እስራት፣ ከፍተኛ የአስተዳደር በደል እንዳለ በማመን ችግሮችን ለመፍታት ቃል በመግባት የማይፈጸም ተስፋ ሰጥቶ የሕዝብን ቁጣ ለማብረድ ለመመለስ ጥረት ማድረግ፣ ከተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች (የእምነተ አሥተዳደር ቡድኖች) ጋር ተደራድሮ ጠባቡን የፖለቲካ ምኅዳር እንደሚያሰፋ ቃል በመግባት ማታለል፣ በተቀሰቀሱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሰላዮቻቸውን አስርገው በማስገባት ንቁ ተሳታፊዎችን፣ ጠቃሚ ሚና የሚጫዎቱትን፣ ድጋፍ ሰጭዎችን፣ ወደ ትግል የወጡትን፣ በከተማ በኅቡዕ የሚንቀሳቀሱትን ማንነት ለይቶ ማወቅና ለቅሞ በመፍጀት ሕዝባዊ ትግሉን ማኮላሸት የመሳሰሉ እርምጃዎችን መውሰድ የሚሉት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እነኝህን እርምጃዎችምሲወስድ ቆይቷል እየወሰደም ይገኛል፡፡

በዚህም መሠረት ወያኔ በከፍተኛ ደረጃ የብአዴን ካድሬዎችን በሀገር ውስጥና በውጭ ባሉ የአማራ ሕዝባዊ እራስን የማዳን ፀረ የጥፋት ኃይል እንቅስቃሴዎች ውስጥ አስርጎ አስገብቷል፡፡ እነኝህ ካድሬዎች ካድሬነታቸው እንዳይታወቅና ፈጽሞ እንዳይጠረጠሩ በጣም አሳቢና ተቆርቋሪ መስለው ለመታየት በአማራ ሕዝብ ዘንድ ተሰምተው የማይታወቁ፣ ከሥነልቡናውና ከማንነቱ ጋር የሚቃረኑ አቋሞችን አዘውትረው በማንጸባረቃቸው ታማኝነትን አግኝተው ቀደም ሲል በተቋቋሙ ድርጅቶች ውስጥ ቦታ ይዘዋል፣ በነዚህ ጽንፈኛ አቋሞቻቸው ዕውቅና እንዲያገኙና አዳዲስ ድርጅቶችን በአማራ ሕዝብ ስም እንዲያቋቁሙ በማድረግም ሕዝቡ ትክክለኛና ታማኝ ድርጅት እንዳያቋቁም ይከላከላሉ፣ መንገድ ይይዛሉ፣ ያዘናጋሉ፣ የትግል አቅጣጫ በማሳት ሕዝቡ ገንዘቡን፣ ጊዜውን፣ ሕይዎቱን በከንቱ እንዲያባክን በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ በእዚህ አዲስ በተቋቋሙ ሐሰተኛ ድርጅቶችና ቀደም ሲል ተቋቁመው በነበሩ የአማራ ድርጅቶች ስምም ትግል ላይና ከተማ ውስጥ በኅቡዕ ያሉ ታጋዮችን የሚረዱ መስለው በመቅረብ ታጋዮችን በማስለቀም፣ በማስመታት ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ሕዝባዊ ትግሉ አሳሳቢ አደጋ ላይ ወድቋል፡፡ የሰዎች ደኅንነትም እንዲሁ አደጋ ላይ እየወደቀ ነው፡፡ ወያኔ የሞት ሽረቱን ነው የዘመተብን፡፡ በዚህ ስልቱ ደግሞ ከፍተኛ ልምድና ብቃት አለው፡፡ እርግጥ ነው ብዙም ባይሆኑ ግፈኛው ወያኔ በአማራ ሕዝብ ላይ በሚፈጽመው ኢሰብአዊ ግፍ ሕሊናቸው ቆስሎ ይሄንን አረመኔያዊ አገዛዝ ከሕዝባቸው ጋር ሆነው ለመታገል የቆረጡ የብአዴን ካድሬዎች አሉ፡፡ ከእነኝህ ካድሬዎችም አሁንም እውስጥ ያሉ አሉ ጥለውም የወጡ አሉ፡፡

ሚናቸውም በጣም ጠቃሚ ነበረ፡፡ ነገር ግን እንደነሱ ሁሉ ተቆርቋሪ መስሎ ሰላዩም ሰርጎ እየገባ ሕዝባዊ ትግሉ ከፍተኛ አደጋ ላይ ወደቀ፡፡ እነኝህ ካድሬዎች ሕዝባዊ ትግሉን ሲቀላቀሉ ከፊሎቹ ብአዴን ውስጥ እንዳሉ ያሳውቃሉ ከፊሎቹ አያሳውቁም፡፡ ሰላዩ የሚገኘው ከማያሳውቁት ወገን ብቻ አይደለም ከሚያሳውቁትም ጭምር ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ ሚናቸው ምንም እንኳ ጠቃሚና አስፈላጊ ቢሆንም አደጋቸው ስለከፋ ከብአዴን ወይም ከወያኔ ጋር ንክኪ ያለውን ወይም የነበረውን ሰው ወደ ሕዝባዊ ትግሉ መቀላቀሉን አሁኑኑ ማቆም ይኖርብናል፡፡ ማቆም ብቻ ሳይሆን

የገቡትንም ማራቅ፣ ማስወጣት፣ መለየት የግድ ይኖርብናል፡፡ በዚህ መሀል ግን ከልባቸው ከሕዝብ ጋር ወግነው ለመታገል የመጡትም የመገለል ዕጣ ሊገጥማቸው ይችላል፡፡ በስንት መከራ የተቀሰቀሰውን ሕዝባዊ ትግል መታደግ ይኖርብናልና ምንም አማራጭ የለንም፡፡ ለሕዝባቸው ለመታገል ያላቸውን ቅንና ቆራጥ ወገናዊ ፍላጎት እናደንቃለን፡፡ ነገር ግን አምላክ አይደለንምና እውነተኛውን ከሐሰተኛው መለየት ስለማንችል በክብር እንሸኛቸዋለን፡፡ እነሱ ግን ይሄንን ችግር ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እዛው ባሉበት ሆነው ከመሰሎቻቸው ጋር እራሳቸውን በማደራጀትና እውስጥ ሆነው በመታገል በራሳቸው መንገድ ሕዝባዊ ትግሉ ለድል እንዲበቃ ማገዝ ይችላሉ ይኖርባቸዋልም፡፡ በመሆኑም ሕዝባዊ ትግሉን ለመታደግ ሁሉም በአማራ ሕዝብ ስም የተቋቋመ ድርጅት ሁሉ እራሱን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከወያኔ ወይም ከብአዴን ጋር ንክኪ ካላቸው ወይም ከነበራቸው ግለሰቦች ሁሉ ማጽዳት ይኖርበታል፡፡ ቀሪዎቹ በኃላፊነት ያሉ ወይም የሚሾሙ ግለሰቦች ማንነት ወይም የኋላ ታሪክም ተብጠርጥሮ የሚታወቅ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይሄንን ስናደርግ ብቻ ነው ሕዝባዊ ትግሉን መታደግ፣ የታጋዮቻችንን ደኅንነትም መጠበቅ የምንችለው፡፡ ይሄንን እርምጃ መውሰድ ካልቻልን ግን እርግጠኛ ሆኘ የምነግራችሁ በሰው ሕይዎት መጫዎት ነው የሚሆነው፣ ትግሉም ምንም እመርታ ሳያስመዘግብ ይጨናገፋል፡፡

በመሆኑም እያንዳንዱ ድርጅት በአስቸኳይ ይሄንን እርምጃ ይውሰድ፡፡ አስቸጋሪ የሚሆነው ብአዴን እንደሆኑ ያላስታወቁትን ወይም እራሳቸውን ያልገለጡትን መለየቱ ላይ ነው፡፡ ለነገሩ እነሱንም ቢሆን መለየት ብዙ የሚያስቸግር አይሆንም፡፡ በንግግራቸው ሳያውቁት የወያኔ ቃላቶችን ይጠቀማሉና በዚህ መያዝ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ "…እንሔድበታለን" የመሳሰሉ የካድሬ ቃላትን በንግግራቸው ይጠቀማሉ፡፡ ወያኔ የብአዴን ካድሬዎችን ውጭ ባለው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በተለይም አሜሪካ ባለው አስርጎ ማስገባት የቻለው ካድሬዎቹን በተለይም በትምህርት (በስኮላር ሽፕ) ስም በመላክ ነው፡፡ በሌሎች ምክንያቶች የሚያስገባቸውም አሉ ዋናው ግን ለትምህርት ብሎ በመላክ ነው፡፡ በአገዛዙ ለትምህርት የተላከ ሰው ካጋጠማቹህ አትጠራጠሩ እሱ የወያኔ ካድሬ ነው፡፡ ወያኔ እንኳንና የውጭ የትምህርት ዕድልን ከፍተኛ ደረጃ ትምህርትን (የዩኒቨርስቲ) ለመማር እንኳ ማንም ሰው አባልነት ካልሞላ በስተቀር መማር እንዳይቻል ካደረገ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ እናም ወገን ሆይ! ይሄንን እርምጃ መውሰዳችን ሙሉ ለሙሉ የወያኔን ሰርጎ የመግባት ዕድል ባይዘጋውም በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሰዋልና ፈጥነን ይሄንን እናድርግ፡፡

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com